# ጤና ይስጥልኝ

**ብ. ነጋሽ 05-28-17**

ኢትዮጵያውያን ሰላምታ ሲለዋወጡ "ጤና ይስጥልኝ" ይላሉ፤ ጤና አትጣ እያሉ ነው። ተለያይተው የቆዩ ወዳጆች ሲገናኙ ጤናን የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎችን ይጠያየቃሉ፤ ከሰዉ አልፈው የከብቱን ደህንነት ጭምር። ኢትዮጵያውያን ተስፋቸውን በጤና ውስጥ ነው አሻገረው የሚመለከቱት፤ "ጤና ከሰጠኝ ለከርሞ . . ." ይላሉ። ይህ ጤና ያለውን ትልቅ ዋጋ ያመለክታል። ኢትዮጵያውያን ከጓሯቸው መድሃኒት አያጡም፤ ደማከሴ፣ ሬሳሃረግ፣ ጤናአዳም . . .። ከቤታቸውም "ድንገተኛ" አይጠፋም፤ ድንገተኛ የሚላመጥ ሃረግ ቢጤ መድሃኒት ነው። እነዚህ ድንገት ለሚያጋጥሙ አጣዳፊ ህመሞች የሚወሰዱ መድሃኒቶች ናቸው፤ እንደማስታገሻም የመስሉኛል።

ኢትዮጵያውያን የዘመናት የእውቀት ጥርቅም የሆነ የህክምናና የመድሃኒት እውቀትም አላቸው። ሆድ ውስጥ የሚረባን ትላትል በኮሶ፣ እንቆቆ፣ መተሬ፣ ቆርሰዲማ፣ . . . ነቅለው ያስወግዳሉ። የተመረዘን ደም በዋግምት መጥጠው፣ በወረንጦ በጥተው ያስወግዳሉ። የተሰበረውን ይጠግናሉ። እንግዲህ እንደው ባህላዊ የጤና አጠባበቅ ስርአቱን ለማስታወስ ያህል ከብዙ እጅግ ጥቂቱን ጨልፌ ጠቀስኩ እንጂ በየብሄሩ ያለው የባህል መድሃኒትና የህክምና ጥበብ ቢዘረዘር መጽሃፍ እንደማይበቃው አውቃለሁ።

ኢትዮጵያውያን መድሃኒትና የህክምና ጥበብ የማወቃቸውን ያህል በሽታም ሲያጠቃቸው ኖሯል። ቀደም ባሉት ዘመናት በሽተኞች ጠያቂ አጠተው ከነቤተሰባቸው እንዲያልቁ የሚያደርጉ ወረርሽኞች የተለመዱ ነበሩ። የኩፍኝ፣ የወባ፣ የማጅራት ገትር፣ መንጋጋ ቆልፍ . . . ወረርሽኞች ደግሞ እስከቅርብ ጊዜም ሲከሰቱ የነበሩ ገዳይ በሽታዎች ናቸው። ኢትዮጵያውያን እነዚህ ድንገት ተከስተው የቻሉትን ያህል አጭደው የሚሄዱ ወረርሽኞች መከላከያው መላ ሲያጡለት ወደመለማመጥ ይገባሉ። በዘፈን ያሞግሷቸዋል፤ "ማርዬ ማር ፍትፍት፣ ታሳምሪያለሽ የልጅ ፊት" እያሉ ለኩፊኝ እነደሚዘፍኑት አይነት። በሰላሙ ጊዜ የክፉ በሽታ ስም አይጠራም፤ ሰምቶ እንዳይመጣ በመስጋት።

ታዲያ እንዲህ ከበሽታ ጋር የተፋጠጠው ህዝብ ዘመናዊ ህክምና እንደሰማይ ርቆት ነው የኖረው። የህክምና ተቋማቱ፤ ክሊኒኮቹ (ጤና ኬላዎች)፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ሆስፒታሎች በከተማዎች አካባቢ የተወሰኑና ጥቂቶች ነበሩ። ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው በገጠር የሚኖር ህዝብ የጤና ተቋማቱን በቀላሉ ተጉዞ ሊደርስባቸው አይችልም። ከህክምና ተቋማቱ መራቅ በተጨማሪ መንገድና የትራንስፖርት አገልግሎት አለመኖሩ ደግሞ ችግሩን አባብሶት ነበር። ህሙማን ወደሃኪም የሚወሰዱት በሽታው በሃገር መደሃኒት ተሞክሮ አልፈውስ ሲል፣ *ከዛሬ ነገ ይሻለዋል* የሚለው ተስፋ ተሟጦ በሽታው ሲጠና ብቻ ነበር። እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ራሱን ችሎ መነቀሳቀስ የማይችለውን ታማሚ፣ ጎበዝ ተሰብስቦ በወሳንሳ ወደከተማ ይወስደዋል። ከተማ ዘመድ ለሌለው ደግሞ ማረፊያው፣ ስንቁም ተጨማሪ ችግር ነበር። በቂ ስንቅና መጠጊያ የሌለው ከበሽታው በላይ ረሃብ፣ ጸሃይና ቁር ያሰቃየዋል። በዚህ ላይ የታካሚው ወረፋ፣ የህክምናው ቀጠሮ መራዘም . . . ችግሩን ያወሳስበዋል። *"ለህክምና መጥቼ ስንቅ አልቆብኝ. . ."* የሚሉ ምጽዋት ጠያቂዎችን ያስታውሷል። እርግጥ አሁን አሁን የመጽዋቾችን ልብ ለማራራት የሚጠቀሙበት ጮካዎች መኖራቸው እርግጥ ነው።

ታዲያ፣ እንዲህ ህክምናና ፈላጊው ተራርቀው በነበሩበት ሁኔታ በርካቶች ሊድኑ በሚችሉ በሽታዎች ህይወታቸውን አጥተዋል። በሰላም መገላገል ይችሉ የነበሩ ነብሰጡር እናቶች ይህችን ዓለም ተሰናበተዋል። ህጻናት በለጋነታቸው ተቀጭተዋል። በቀላል መድሃኒትና ክትባት መታከምና መከላከል የሚቻል ወረርሽኝ አርሶ አደሩን በእርሻ ስራ ወቅት አስተኝቶ ሃገርን ለረሃብ አጋልጧል። ቤተሰቦች አልቀው ጎጆዎች ተዘግተዋል።

ይህን የኢትዮጵያ ህዝብ የተጋፈጠውን የጤና ችግር የመፍታት ጉዳይ የዜጎችን በህይወት የመኖር መብት የማረጋገጥ ጉዳይ ነው። ጤናማ ዜጋ እንዲኖር ማድረግ አምራች ዜጋ እንዲኖር የማድረግ ጉዳይ ነው። ጤናማ አምራች ዜጋ ከሌለ የሃገርን ኢኮኖሚ በማሳደግ ለዘለቄታው የህዝብን ኑሮ ወደተሻለ ደረጃ የማሸጋገር ጉዳይ የህልም እንጀራ ነው። በመሆኑም በተለይ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የጤና ጉዳይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል። ድንቅ ውጤትም ተመዝግቧል።

ከአንድ ተኩል አስርት ዓመታት በፊት በሃገሪቱ የወባ ወረርሽኝ ክስተት የተለመደ ነበር። በዚህ የወባ ወረርሽኝ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች የሚያልቁበት ሁኔታ ነበር። የወባ ወረርሽኝ ይከሰት የነበረው በሩቅ የሃገሪቱ አካባቢዎች ብቻ አልነበረም። ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኙና በሌሎች ትላልቅ የሃገሪቱ ከተሞችና በዙሪያቸው ጭምር እንጂ። አንድ ተኩል አስርት ዓመታት ወደኋላ ተመልሰን በወባ ወረርሽኝ ላይ ያሉ መዛግብትን ብናገላብጥ፣ ከአዲስ አበባ 100 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ትልቋ ከተማ - አዳማ፣ በአማራ ክልላዊ መንግስት ርዕስ ከተማ ባህርዳርና በዙሪያቸው የወባ ወረርሽኝ ተከስቶ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ሰዎች መሞታቸውን መረዳት እንችላለን።

በአሁኑ ጊዜ የወባ ወረርሽኝ ክስተትን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ተችሏል። ወባ በወረርሽኝ መልክ የሚከሰትበት ሁኔታ አክትሟል። ኢትዮጵያ እ ኤ አ በ2030 ወባን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ከሚችሉ የዓለም ሃገራት አንዷ ትሆናለች ተብሎ ይጠበቃል። ከወባ በተጨማሪ የማጅራት ገትርና የፖሊዮ ወረርሽኝን መቆጣጠር ተችሏል። ባለፉት አስር ዓመታት ፖሊዮና ማጅራት ገትር በወረርሽኝ መልክ አልተከሰቱም።

ወረርሽኝን ከመከላከል ባሻገር በጨቅላ ህጻናት፣ ከአምስት ዓመት በታች ባሉ ህጻናትና በእናቶች ሞት ቅነሳ ድንቅ ውጤት ተመዝግቧል። ከሃያ ስድስት ዓመት በፊት ከሚወለዱ1 ሺህ ህጻናት 182ቱ ይሞቱ ነበር። አሁን ይህን የጨቅላ ህጻናት የሞት መጠን ወደ 29 መቀነስ ተችሏል። ከሁለት ተኩል አስርት ዓመታት በፊት ከአምስት ዓመት በታች ከሚገኙ 1 ሺህ ህጻናት 160 ያህሉ ይሞቱ ነበር። አሁን ይህን የህጻናት ሞት ወደ 60 ማውረድ ተችሏል። በእናቶች ሞት ቅነሳም ተመሳሳይ ድንቅ ውጤት ተመዝግቧል። ከሃያ ስድስት ዓመታት በፊት ከ1 መቶ ሺህ ወላድ እናቶች 1 ሺህ 4 መቶ ይሞቱ ነበር። አሁን ይህ የወላድ እናቶች የሞት መጠን ወደ 412 ቀንሷል። ኢትዮጵያ በእናቶችና በህጻናት ሞት ቅነሳ እ ኤ አ ከ2000 እስከ 2015 ዓ/ም ለአስራ አምስት ዓመታት ተግባራዊ የተደረገውን የተባበሩት መንግስታት የልማት ግብ ካሳኩ ሃገራት አንዷ ነች። ኢትዮጵያ ይህን የልማት ግብ ያሳካችው ከጊዜው ቀድማ ነበር።

ባለፉ ዓመታት በጤና ተቋማት መስፋፋትና በህክምና ባለሙያዎች ቁጥር እድገት የተመዘገበውም እድገት ከፍተኛ ነው። ከሃያ ስድስት ዓመት በፊት የሃገሪቱ ሆስፒታሎች 72 ብቻ ነበሩ፤ አሁን የሆስፒታሎች ቁጥር (የግል ሆስታሎች ሳይጨመሩ) 310 ደርሷል። ከሃያ ስድስት ዓመታት በፊት በሃገሪቱ የነበሩ የጤና ጣቢያዎች 153፣ ክሊኒኮች (የጤና ኬላዎች) 2230 ብቻ ነበሩ። አሁን የጤና ጣቢያዎች ቁጥር ወደ 3500 አድጓል፣ የጤና ኬላዎች ቁጥር ደግሞ ከ16 ሺህ በላይ ደርሷል።

የህክምና ባለሞያዎችን ቁጥር ስንመለከት፤ ከሃያስድስት ዓመታት በፊት በሃገሪቱ የነበሩት የህክምና ዶክተሮች ቁጥር 1 ሺህ 2 መቶ ብቻ ነበር። ሃገሪቱ አሁን 9 ሺህ ገደማ የህክምና ዶክተሮቸ አሏት። 3 ሺህ 5 መቶ ገደማ የነበረው የነርሶች ቁጥር ወደ 46 ሺህ አድጓል። 29 ብቻ የነበረው የጤና መኮንኖች ቁጥር ከ6 ሺህ በላይ ደርሷል። ከሃያስድስት ዓመታት በፊት 7 ብቻ የነበሩት የሃገሪቱ የጤና ማሰልጠኛ ተቋማት አሁን 35 ደርሰዋል።

ከዚህ በተጫሪ በተለይ በአርሶ አደሩ መንደር በር ከበር እየተንቀሳቀሱ የመሰረታዊ ጤና አጠባበቅ አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች በመላ ሃገሪቱ ተሰማርተዋል። የጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎቹ ከ40 ሺህ በላይ ናቸው። እነዚህ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች በተለይ የንጽህና አጠባባቅ ስርአትን ለአረሶ አደሩ በማስተማር በንጽህና ጉድለት የሚመጡና በሃገሪቱ የጤና ችግር ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸውን በሽታዎች መከላከል አስችለዋል። ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል የጤና ተቋማት ባለመስፋፋታቸው ያልዳበረውን የጤና ተቋማትን አገልግሎት የመጠቀም ልምድ በማሻሻል ረገድ ትልቅ ድርሻ ተጫውተዋል። ነብሰጡር እናቶች የሃኪም ክትትል እንዲያደርጉ በመምከርና በማነሳሳት በጤና ጣቢያ የሚወልዱ እናቶች ቁጥር እንዲጨምር፣ በዚህም የእናቶች ሞት ቁጥር እንዲቀንስ ትልቅ አስተዋጽ አበርክተዋል።

ባለፉት ሃያ ስድስት ዓመታት የሃገሪቱ አጠቃላይ የጤና ሽፋን ከ38 በመቶ ወደ መቶ በሙቶ ማደግ ችሏል። አሁን ከህክምና አገልግሎት ሽፋን ውጭ የሆነ የሃገሪቱ አካባቢ የለም። የህዝቡ አማካይ እድሜ ከሃያ ሰድስት ዓመታት በፊት ከነበረበት 46 ወደ 64 ዓመት ከፍ ብሏል። የዜጎች አማካይ በህይወት የመኖር እድሜ በዚህን ያህል ከፍተኛ መጠን የተሻሻለው በቀዳሚነት በሃገሪቱ የጤና አገልግሎት በመስፋፋቱ ነው።

እንግዲህ፣ የኢፌዴሪ መንግስት መከላከል ላይ የተመሰረተ የጤና ፖሊሲ ቀርጾ ተግባራዊ ባደረገባቸው ያለፉ ሁለት አስርት ዓመታት ከላይ በአጭሩ የተጠቀሰውን ስኬት ማስመዝገብ ችሏል። ይህ ስኬት “ጤና ይስጥልኝ” እያለ ጤናን በመመኘት ሰላምታ ለሚለዋወጠው የኢትዮጵያ ህዝብ የጤና ምኞቱን እውን ማደረግ አስችሏል። የጤና ምኞታችን ስኬት የግንቦት 20 ድል ፍሬ ነው።